# እየሞቱ መኖር ቢበቃንስ

ከጀ.ዘ.ማሪ

አዲስ አበባ 12ኛውን የዓለም ፓርላማዎች ጉባኤን አስተናዳለች የገኘው ፓርቲ አፍነ እጅ እና እግር ሆኖ የሚያገለግለው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አርማውንምነ ዜናውንም ይዜውን የፓርላማዎች ስብሰባ አድርጎ ነው የሰነበተው የቴሌቭዥኑ ጋዜጠኞች ሲቃ እስኪተናነቃቸው ድረስ ዘግበዋል፡፡ አዘጋገባቸው ግን ጌቶቻቸው ምን ያህል እንደተደሰቱባቸው እና የፖለቲካ ትርፍ እነዳስገተኙላቸው እያሰሉ ነው የሚመስለው፡፡

ከላይ የጠቀስኩትን ለማስረዳት አንድ ነገር ብቻ ማቅረብ በቂዬ ነው፡፡ የቴሌቪዥኑም ሆነ የሬድዮ ጋዜጠኞች ያስተላለፉት አንድ ዓግና ዘገባ የአዲስ አበባ ፎቅ በፎቅ መሆን እና የተለያዩ ሆቴሎች መገንባት ተሳታፊዎች ካላቸው አድናቆት እና አስተያየት ጋር እየተደባለቀ እስከሚታክት መቅረቡ ነው ይሄም ሆድ ሲያውቅ ----ነውና ነገሩ እሰይ ለአዲስ አበባ ዕድገታችን የውጭ ዜጎች መሰከሩ ብለን እንድናስብ ተሰልቶ ከሆነ ተሸውደዋል፡፡

እውነት ግን እንደግን ነው እንዴ? እየኖርን ነው እንዴ? በጥቂት ቱጃር ግለሰቦች እና በእከክልኝ ልከክልህ ተጠቃሚዎች የተገነቡ ብዙ ህንፃዎች የብዙሃኖችን መለወጥ ምሳሌ ናቸው እንዴ? ህንፃዎችን መኮነኔ ሳይሆን የከተማ ሀብትነታቸውን ማንኳሰስ ፈልጌም ሳይሆን የመለወጣችን መለኪያዎች ሊሆኑ አይችሉም እያልሁ ነው፡፡ ፎቆችን አጅብ የሚኖሩ ደሃዎች እና ጦም አዳሪዎች ኑሮአቸው ካልተቃናነ በየጎዳናው ለምፅዋት የሚዘሩጉ መዓፎች ካልተሰበሰቡነ የሀብት ልዩነት በደሃው እና በሀብታሙ መካከል ለከቱን እስከሚያጣ ተለጥጦ እና አንዱ በይ ሌላው ተመልንች በሆነበት ነገር ቆም ብሎ ማሰብ የእንድ ፈንጅ እሴ ብዙ ፎቅ አላችሁ አለን ብሎ ባደባባ መናገር የሚያሳፍር ነው፡፡

በኢትዮጵያችን ያሉት የኤፍ-ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎችም ቢሆኑ ማህበራዊ መታደስ ሊፈጥሩ የሚችሉ ፕሮግራሞችን ሰርተው አያውቁም፡፡ በተሰጣቸው ትንህ ቀዳዳ ሲንፈራገጡ ተደናግረው ሲያደናግሩ ይውላሉ፡፡ ኤፍ -ኤም ሬዲዮ የራሱ ፎርማት እንዳለው ብገነዘብም የኢህአዴግ ጉዳይ ሲሆንባቸው ሙዚቃውንም መዝናኛውንም ሰርዘው ሳለ ሊግ ምስረታነ ሰለ ፎረም መዋቅር ሲዘረዝሩ መመልከቱ እንድታዘባቸው አድርጎኛል፡፡

ሌላው የተጠመዱበት ተግባር ስፖርት ነው፡፡ ወጣቱ ስለ ሀገሩ እና ስለተጫነበት ችግር እንዳያስብ ጭንቀቱ ፕሪሚየር ሊግ እና ሻምፒዮንስ ሊግ እንዲሆን ይተጋሉ፡፡ ስለዚህም እግር ኳስ መዝናኛ መሆኑ ቀርቶ ለወጣቱና ለሽማግሌውም ጭንቀት እና ህይወት እስከመሆን ደርሷል፡፡ ሬዲዮኖቻችን ለከስ እነደተጉት ማሸበረሰብ ያለበትን የህይወት ጫና በገልፅ እና ካለፍርሃት እንዲወያይ ቢጋብዙ የአከሌ ተጫዋቾች እጮኛ አኮረፈች ምን ይበጃል? እከሌ የሚባል ተጫዋቾች እግሩን ወለም አለውነ የአከሌ አክስቱ ሰለሞቱ አይሰለፉም አይነት ተልካህ ውይይቶች ዘወትር ይደረጋሉ፡፡ ----- ነገር ግን ትንፋሽ አይሉም፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በሚሊኒየም አዳራሁ የሰበሰቧቸወው አድር ባይ እና እቢላ ላይ ሰባት ሺህ ወጣቶች (በምንም መመዘኛ የኢትዮጵያን ወጣት ሊተኩ እንደማይችሉ ይሰመርልኝ) ጠንካራ ሀገራዊ ጥያቄ ማንሳት ተስኗቸው በፍርሀት ሰወላከፍ እንዴውም ለጠቅላይ ሚኒስቴሩ ጤና እና እረጅም ዕድሜን ከ ሺ ዓመት ንግስና ጋር ሲመኙ አስተውለናል:: ለጥቀም ብለው ነው ብሎ መከራከሩም እሩቅ አያስኬድም ነገር ግን በውርደት እየኖሩ ዘመንን መግፋት ከመልመድ የመጣ ነው ቢባል ይሻላል:: ወይም እየሞቱ ጠቅልሎ ከሀገር ወጥቷል:: በሌላ ገፅ ደግሞ ህይወቱን ወይም የመኖር ዓለሙን ገዥዎች ስይረው በሰጡት ልክ ወስኖ በአድርባይነት አድርባይነት እያጎበደደ የሚኖረው ሀገሩን አጥለቅልቆታል::

ፅሁፍ የመነሻ ፈሩን ስቶ እያዘመመ እነደሄደ ብገነዘብም ሌላው ሳልጠቅሰው የማላልፈው ጉደይ አብዛኛው ሰው በአደባባይ ኢህአዴግን እንደሚደግፍ ሲናገር ሰሞቹ አለማወቁ ነው:: የተለመደው ብቸኛ ነገር ማዝምረም ብቻ ነው እየተቃወሙ ተቃውሞን በሆድ አምቆ መኖር------ ይሄ አስከፊው የፖለቲንዊ ሹቀታችን አካል ነው:: ማንም ሰው በማለት በሚያስደፍር መልኩ ኢህአዴግ ስለሚያደርገው እስር፣ ሰብዓዊ መብት ጥሰት እና ወከባ ካፌ ውስጥ ለመወያየት ብትሞክር እንደ ነባር ጫሪ ያዩሀል ወይም ጎመን በጤና ወዳጀ የሉሄል ያጋጠመህ ሰው በጣም ደፋር ከሆነ ደግሞ ቢያንስ እንከ ግራ እና ቀኙን ተገላምጦነ ድምፁን ዝቅ አድርጎ «ጌታዬ እነዚህ ሰዎች ዘላለም መንገስ ነው ፍላጎታቸው ተቃዋሚዎችን እያዋከቡ ለውጪው ሰው እያስመሰሉ መኖር ነው የሚፈልጉት:: ዴሞክራሲው ጭምብል እንጂ ዴንታ የላቸውም» ሊልህ ይችላል እንግዲህ እየሞቱ መኖር ማለት ይህ ነው::

ለምን ብሎ መጠየቅ ለየተለመደ አይደለም:: ለምሳሌ በ2000ዓ.ም በአንድ ብር ይሸጥ የነበረ አንድ እንጀራ 3 ብር በ2001 ዓ.ም ገብቷል ሌሎች ሸቀጣ ሸቀጦችም በ2 እና 3 እጥፍ ጨምረዋል:: ግን ህዝቡ ዝም ብሏል:: መብራት በሳምንት ሁለት ጊዜ ይጠፋል ዝም! ----- ድብታ ------- አዲስ አበባ ብሔራዊ ድንዛዜ ወርሷታል:: ሰው ተንበርክኮ መኖርን ተላምዷል:: ቢያንስ እንከ በጥቂቱ ሲሰላ ያለመግዛት አድማ በማድረግ ተቋውሞን መግለፅ ይቻል ነበር ግን ዝምታን ተመርጧል::

ዋጋ ጨመረ ሲባል የሚቀድመው ጥያቄ ለምን? ነበር ግን ዝምታ ተመርጧል:: ሆኖም ተብድሮም ሆነ ተለቅቶ ለመግዛት ሰልፍና እሽቅድድሙ ሌላ ነው:: ነዳጅ ጨመረ ሰልፍ፣ጨው ጨመረ ሰልፍ፣ የፋሲካ ዶሮ ለመግዛት ሰልፍ፣ ለእንቁላል ሰልፍ፣ ውሃ ጠፋ ሰልፍ፣-------------

ድፍረት ካልሆነብኝ እንደኛ ህዝብ ዋጋ ሲጨምር ለመግዛት የሚጓጓ በዓለም ላይ ያለ አይመስለኝም:: ህዝቡ ይህን ገበያ የማራገቢያ የሰልፍ ልማዱን መንግስት ሲሳሳት ቢጠቀምበት ኖሮ ዛሬ ለውጥ እናይ ነበር::

እኛ መሞት ስንጀምር ሀገር ትሞታለች:: በአስቸኳይ ከወረስን ዱብታ መንቃት ይጠበቅብናል:: ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት የሀገራችን ጉዳይ የሁላችንም ጉዳይ ነው:: ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም እንዳሉት ያለው ምርጫ አንድ ነው ታግሎ የተሻለች ኢትዮጵያን መፍጠር ምክንያቱም አንዴ ኢትዮጵያዊ ሆነን ተፈጥረናልና::